# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 59 ጥቅምት 11 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## <<ሴቶች የሌሉበት የፖለቲካ ድርጅት ምንም ነው!>>

## <<ኢዜማ፣ ለምርጫ ከሚያቀርባቸው ዕጩዎች መሀል 30 በመቶና ከዛ በላይ የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ እየሰራ ይገኛል>>



የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ

# ቆይታ

## ‹‹ሴቶች የሌሉበት የፖለቲካ ድርጅት ምንም ነው!››

## ‹‹ኢዜማ፣ ለምርጫ ከሚያቀርባቸው ዕጩዎች መሀል 30 በመቶና ከዛ በላይ የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑእየሰራ ይገኛል››

የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ

የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ገነት አራጌ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ተምረው ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡ በኢዜማ ውስጥ ባለው አደረጃጀት የምርጫ ወረዳ 17 ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የፖለቲካ ጅማሮ ያደረጉ ሲሆን በቅርቡ በብሔራዊ የሥራ አስፈጻሚ ደረጃ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ በመሆን ከተመረጡት ሴቶች መሀል አንዱ ናቸው፡፡ የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ ‹‹የቆይታ›› አምድ እንግዳ ናቸው፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነውን አጠር ያለ ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ መልካም ንባብ!



*ኢዜማ ከሌሎች ፓርቲዎች አንጻርበሴቶች ላይ ምን አይነት ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል?*

ኢዜማ ሴቶችን ለቁጥር ማሟያ ብቻ አይደለም የሚፈልጋቸው፡፡ መምረጥ፣ መመረጥ፣ እንዲሁም ፖሊሲ መቅረፅ የሚችሉ ጠንካራና ብቁ የሆኑ ሴቶች እንዲኖሩ ስልጠና በመስጠት አቅም የመገንባት ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ፓርቲዬ ሴቶች ከፖለቲካ መጠቀሚያነት በዘለለ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ለማድረግ ተግቶ እየሰራ ነው፡፡ በቀረፃቸው 45 የሚሆኑ የፖሊሲ ሰነዶች ላይም ሴቶች እንዲሳተፉ በር ከፍቷል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ካስቀመጠው ኮታ በተጨማሪም እጩ ሴት ተወዳዳሪዎች እንዲኖሩና በምርጫም አሸንፈው እንዲወጡ ስልጠና በመስጠት የአቅም ግንባታ ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡

*በበለጠ ትኩረት የምታረጉባቸው ዐበይት ነገሮች ምን ምን ናቸው?*

መጪው ጊዜ ምርጫ እንደመሆኑ መጠን ብዙ ጊዜያችንን ምርጫ ላይ እናደርጋለን፡፡ ትልቁን ትኩረታችንን የምናደርገው ብቁ እና ተወዳድረው ማሸነፍ የሚችሉ ሴቶችን በእጩነት ማቅረብ ላይ ነው፡፡

*ሴቶች በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ በሰፊው እንዳይሳተፉ እያደረጓቸው ያሉ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? ይሄን ለመቅረፍ ምን ማድረግ ይገባል?*

በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ የተመለከትን እንደሆነ ጠንካራና ውሳኔ ሰጪ ሴቶች እናገኛለን፡፡ ለአብነት ያህልእንደእቴጌጣይቱ ያሉሴቶችንመጥቀስ ይቻላል፡፡የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እንኳን በቤት ውስጥ ኃላፊነት ላለባቸው የሀገራችን ሴቶች፣ ለወንዶችም እንኳ የማይነካ እንደ ጋለ ብረት የሚያስፈራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም ምክንያት ሴቶች ፖለቲካውን ለመቀላቀል ተቸግረዋል፡፡ያሳለፍናቸው የፖለቲካ ተሳትፎዎች በመታሰር፣ በመሰደድ እንዲሁም በግድያ በመታጀቡ፣እንዲሁም የማኅበረሰቡን ጫና ሰብሮ መውጣት አለመቻላችን የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

ሌላው ዋናው ችግር በሀገራችን ሴቶቻችንን ያላሳተፈ የፖለቲካ ሥርዓትመኖሩ ነው፡፡ አሁን ተቀይሯል በሚባለው የፖለቲካ ሥርዓት እንኳን ሴቶችን ለፖለቲካ ትርፍ ብቻ ሥልጣን እንዲወጡ ነው የሚደረገው፡፡

*መፍትሔ ተብሎ ሊቀመጥ የሚችለው ምንድን ነው?*

በመጀመሪያ ማኅበረሰቡ ስለ ሴቶች እና ስለ ፖለቲካ ያለውን አመለካከት በትምህርት መቀየር አስፈላጊ ነው፡፡የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ማሳወቅ ይገባል፡፡ ስለዚህም መሪዋን የመምረጥና መሪ የመሆን፣መብቷን ማስከበር እንደምትችል እና ማኅበረሰቡ ለፖለቲካ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት በተደጋጋሚ ▶ ስልጠና እና ትምህርት በመስጠት መለወጥ አስፈላጊ ነው፡፡

የሴቶች ሹመት ከፖለቲካ ትርፍ ይልቅ በእውቀት እና በብቃት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ ሥልጣን ላይ ያሉ ወይም የሚወጡ ሴቶች የሴቶችን ችግር የሚረዱና ባሉበት ቦታ ሁሉ ሴቶችን መረዳት እና መርዳት እንዳለባቸው ማስተማር ይገባል፡፡

*ዘንድሮ ይካሄል ተብሎ የሚጠበቀውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ሴቶች በተመራጭነትም ሆነ በመራጭነት በጉልህ እንዲሳተፉ በኢዜማ በኩል ምን አይነት ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛል?*

ኢዜማ ሴቶች 30% እና ከዛ በላይ በምርጫው ተወዳደሪ ሆነው እንዲቀርቡ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህንንም ቁጥር ለማሟላት ከቀበሌ አንስቶ እስከ ሀገር አቀፍ ደረጃ ሥልጠና በመስጠት እና በተለያዩ ድጋፍ የማድረጊያ ስልቶች የማደራጀትና የማስተማር ሥራ እየሰራ ይገኛል፡፡

መራጮችን በሚመለከት ማንኛውም እድሜዋ የደረሰ ሴት ነጻ ሆና ያለፍርሃት መሪዋን በመምረጥ የራስዋን እድል በራስዋ መወሰን እንድትችልና ሌላ ሰው በመረጠላት መሪ መተዳደር እንደሌለባት አበክረን እናስተምራለን፡፡

*ኢዜማን ወክለው ሴቶች ለመወዳደር ቢፈልጉ ምን ምን መስፈርት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል?*

ኢዜማን በመወከል ምርጫ ለመወዳደር የምትፈልግ ሴት ማሟላት ያለበት መስፈርት 21 ዓመትና ከዛ በላይ መሆን፣ ዜግነቷ ኢትዮጵያዊት የሆነች፣ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብቷ በሕግ ያልተገደበች፣ የእጩና ድጋፍ ምልመላ ኮሚቴ ያወጣውን መስፈርት (የትምሕርት ደረጃ፣ የፖለቲካ ተሞክሮ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ ተቀባይነት ወዘተ...) የምታሟላእስከሆነች ድረስ ኢዜማን ወክላ በምትኖርበት የምርጫ ተወዳዳሪ እጩ ሆና መቅረብ ትችላለች፡፡

*የሴቶችን አቅም ከማጎልበት አንጻር ምን የሰራችሁት ሥራ አለ? በቀጣይስ ምን ለመሥራት አስባችኋል?*

የተለያዩ ሥልጠናዎችን በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ የምርጫ ወረዳዎቻችን ላሉ ሴት ተጠሪዎችና አባላት መስጠት ጀምረናል፡፡የአዲስ አበባ ስልጠናዎችን እንዳጠናቀቅን በሁሉም የኢዜማ አደረጃጀት ባሉ የምርጫ ወረዳዎች ከሌሎች ዘርፎች (የሙያ ማኅበራት፣ብሔራዊ የወጣቶች ጉዳይና የድርጅት ጉዳይ)ጋር በመቀናጀት ስልጠናዎችን የምንሰጥ ይሆናል፡፡

*ለኢዜማ እዚህ መድረስ የሴቶች ድርሻ እንዴት ይገለጻል?*

ሴቶች የሌሉበት የፖለቲካ ድርጅት ምንም ነው፡፡ የፖለቲካ ድርጅት ብቻ ሳይሆን የትኛውም ዘርፍ ሴቶችን እስካላሳተፈ የትም መድረስ አይችልም፡፡ ዛሬ ኢዜማ ለቆመበት ቦታ የሴቶች ተሳትፎ ከፍተኛ ነው። ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉ፣ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊት ሴቶች ያሉበት ድርጅት ነው፡፡ ከምስረታው አንስቶ አሁን ያለበት ደረጃ ድረስ አባላትን በማደራጀት፣ በመመልመል፣ ፖሊሲዎችን በመቅረጽና ጥናቶችን በማካሄድ ሴቶች ትልቅ አስተዋፅኦ ተጫውተዋል፡፡

*ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?*

በመጨረሻ ለሴቶች ማለት የምፈልገው ከፖለቲካ መጠቀሚያነት ወጥተን የራሳችንን እጣ ፋንታ ራሳችን መወሰን የምንችል፣ መምረጥና መመረጥ የምንችል፣ ጠንካራና ውሳኔ ሰጪዎች መሆን እንዳለብን ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

*ከእኛ ጋር ቆይታ ለማድረግፍቃደኛ ስለሆኑ በዜጎች መድረክ ስም አመሰግናለሁ፡፡*

ለሰጣችሁኝ እድል እኔም አመሰግናለሁ፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ጥቅምት 11 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# < <የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለመቆጣጠር፣ ለማዘመንና ለማሰልጠን አዲስ አበባ ወሳኝ ነች> >

## አንዷለም አራጌ

ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምክትል መሪ አንዷለም አራጌ የሚቀጥለውን ምርጫ በብቃት እና አርአያነት ባለው ሁኔታ ለመወጣት ፓርቲያቸው ዝግጅት እያደረገ እንዳለ ገለጹ፡፡

ምክትል መሪው ባሳለፍነው ሳምንት ቅዳሜ ጥቅምት 7 ቀን 2013 ዓ.ም በመስፍን ወልደማርያም አዳራሽ ከአዲስ አበባ 23ቱም ወረዳዎች ለተውጣጡ የኢዜማ የምርጫ አስተባባሪዎች ስልጠና መክፈቻ መርሀ ግብር ላይ በመገኘት ባደረጉት ንግግር ላይ ይህን የተናገሩት፡፡

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ተሞክሮ አለመሳካቱን ያስታወሱት ምክትል መሪው ለዚህ የመንግሥት ሚና ዋና ቢሆንም ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ጉድለት እንዳለበት ተናግረዋል፡ ፡ ‹‹የተፎካካሪ ፓርቲዎችስ የሚገባንን ዝግጅት አድርገናል? ብለን ብንጠይቅ የፓርቲዎችም ጉድለት ብዙ ሆኖ እናገኘዋለን›› ያሉት አንዷለም አራጌ፣ ፓርቲያቸው ኢዜማ ያንን ጉድለት ሞልቶ አባላቶቹን አንቅቶ አሰልጥኖ የሚቀጥለውን ምርጫ በብቃት እና አርአያነት ባለው ሁኔታ ለመወጣት ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ጥቅምት 07 ቀን 2013 ዓ.ም እና ጥቅምት 08 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበበ ከተማ ለሚገኙ የምርጫ ወረዳ አስተባባሪዎቹ የሰጠው ስልጠናም የዚህ ዝግጅት አንድ አካል መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ምክትል መሪው በንግግራቸው አዲስ አበባ ለምርጫም ሆነ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ያላትን ወሳኝነትም በስፋት አብራርተዋል፡፡ ‹‹አዲስ አበባ በአጠቃላይ ለምርጫም ሆነ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ በጣም ወሳኝ ከተማ ናት፡፡ ምትሀታዊ ቀመሩ (magic formula) የሚገኘው ከአዲስ አበባ ጋር ተያይዞ ነው›› ያሉት ምክትል መሪው አዲስ አበባ ከተማ በምርጫ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ከተማ መሆኗን ተናግረዋል ፡ ‹‹የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለመቆጣጠር፣ ለማዘመንና ለማሰልጠን አዲስ አበባ ወሳኝ ነች›› ሲሉ የተደመጡት ምክትል መሪው ፓርቲያቸው የሰጠው ስልጠና ለሰልጣኞች ስለ ኢዜማ ግንዛቤ የሚያስጨብጥና የስልጠናው ተካፋዮች ለሚከውኑት የማደራጀት ሥራ የሚረዳ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥቅምት 07 እና 08 ቀን 2013 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ ለተውጣጡ የምርጫ ወረዳ አስተባባሪዎቹ የሰጠው ስልጠና ከሱማሌ፣ ቤንሻንጉል፣ አፋር፣ ሐረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ፣ ሲዳማና አማራ ክልል እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ለተውጣጡ ሰልጣኞች የሰጠው ስልጠና ቀጣይ መሆኑን ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡





# የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ

ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ቀጣዩን አገር አቀፍ ምርጫ አስመልክቶ ከጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በ27 ዞኖች ለሚሰጠው ስልጠና ከማዕከል ለተውጣጡ አሰልጣኞች ረቡዕ ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም በዋናው ጽ/ቤቱ ስልጠና መስጠቱን የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

እንደ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገለጻ የአሰልጣኞች ስልጠናው የምርጫ ወረዳዎች ቀጣዩን ሀገር አቀፍ ምርጫ እንዴት በብቃትና በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ተሳትፎ አድርገው ውጤት ማምጣት ይችላሉ በሚል ጭብጥ ላይ መሰረት ያደረገ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ ኃላፊው ሰልጣኞች በስልጠና ማንዋሎች በመታገዝ ከ435 ወረዳዎች ለሚወከሉ 1300 የወረዳ አመራሮች በ27 ዞኖች ስልጠናው ከጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ እንደሚሰጡና አሰልጣኞች ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ የስልጠና ቁሳቁሶችን በመያዝ ወደ ተመደቡባቸው ቦታዎች እንደሚያመሩ አስረድተዋል፡፡ ለዚህም ቅድመ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን የጠቆሙት ኃላፊው ከአንድ የምርጫ ወረዳ ሊቀመንበር፣ የድርጅት ጉዳይ፣ የሕዝብ ግንኙነትና የፋይናንስ ኃላፊዎች በድምሩ አራት አመራሮች የስልጠናው ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ ጠቁመዋል፡፡

ከዞን ስልጠናው መጠናቀቅ በኋላ የምርጫ ወረዳ ሰልጣኞች በየወረዳቸው በመውረድ ለአባላትና ለቀሪ ሥራ አስፈጻሚዎች ስልጠና ይሠጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

# ኢዜማ፣ ከመላው ሀገሪቱ ለተውጣጡ የምርጫ አስተባባሪዎቹ ሲሰጠው የነበረውን ስልጠና አጠናቀቀ

ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከመስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከመላው የሀገሪቱ ክፍል ለተውጣጡ የዞን አስተባባሪዎች በምርጫ ስትራቴጂ ማኔጅመንት ካውንስል አዘጋጅነት በድርጅት ጉዳይ አስተባባሪነት በተለያየ ዙር ሲሰጥ የነበረውን ስልጠና እሁድ ጥቅምት 08 ቀን 2013 ዓ.ም አጠናቀቀ፡፡

የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ካውንስል በሥሩ ሰባት ዘርፎችን አቅፎ የያዘ ኮሚቴ ሲሆን እነዚህም የእጩዎች ምልመላና ደጋፍ ዘርፍ፣ የመንግስታዊ ጉዳዮች ዘርፍ፣ የፕሮግራም፣ ፓሊስና ማኒፌስቶ ዘርፍ፣ የምርጫ የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ፣ የምርጫ የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ፣ የምርጫ ግብዓት አሰባሳቢ ዘርፍና የምርጫ የጽህፈት ቤት ድጋፍ ናቸው። በስልጠናው የእጩዎች ምልመላና ድጋፍ፣ የድርጅት ጉዳይ፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ የምርጫ ግብዓት አሰባሳቢ እንዲሁም ፖሊሲና ማኒፌስቶ ዘርፎች ስልጠና ሰጥተዋል፡፡

ስልጠናውን መስጠት የጀመረው የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ ሲሆን የድርጅት ጉዳይ ዘርፍ የምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻን መሸከም የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዴት ማድረስ ይቻላል? ወደ ምርጫ ከመገባቱ በፊት የምርጫ ወረዳዎችን አቅም እንዴት መገንባት ይቻላል? 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ለኢዜማም ሆነ ለሀገሪቷ ያለው ፋይዳ ምንድነው? ኢዜማ ሀገር አቀፉን ምርጫ እንዴት ነው የሚመለከተው? የሚሉ ነጥቦች በስልጠናው ከዳሰሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች መሀል ይገኙበታል፡፡

ከድርጅት ጉዳይ በማስከተል የሕዝብ ግንኙነት ዘርፍ እና የሀብትና ግብአት አሰባሳቢ ኮሚቴ ስልጠናቸውን የሰጡ ሲሆን የኢዜማ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ ስትራቴጂክ ግቦች ምንድናቸው? የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ምን ምንን ያካተተ ነው? የምርጫ ስርአት ሲባል ምን ማለት ነው? የምርጫ መርሆች የሚባሉትስ ምንድናቸው? የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ምን መምሰል አለበት? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

ብሔራዊ የበጀትና ፋይናንስ ሰብሳቢው አንድነት ሽፈራው የኢዜማ ራዕይ፣ አላማና ግብ እንዴት ማሳካት እንደሚቻል ማብራሪያቸውን ሲያቀርቡ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና ራሳቸውንና ማኅበረሰቡን ሊደግፉ የሚችሉ ዕጩዎችን በማቅረብ ለማኅበረሰቡ በአግባቡ በማስተዋወቅ እንዴት የምርጫ ዘመቻውን የተሳካ ማድረግና ጠንካራ ፓርቲም መፍጠር እንደሚቻል ለስልጠናው ተካፋዮች አስረድተዋል፡፡

በእጩ ምልመላ ዘርፍ በተሰጠው ስልጠና የእጩዎች ምርጫ ግብ፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መስፈርት፣ የብቁ እጩዎች ፍለጋ አቅጣጫ፣ የእጩዎች ምርጫ የሃላፊነት ድርሻዎች፣ የቅሬታ አፈታት መርሆችና አጠቃላይ የእጩዎች ምርጫ ሂደት የሚሉ ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡

የእጩ ምልመላና ድጋፍ ኮሚቴ ሰብሳቢው ኢዮብ መሳፍንት ጠንካራ ዕጩዎችን ማቅረብ ያለውን ፋይዳ አስረድተዋል፡፡

ስልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላም ሰልጣኞች ከኢዜማ ጋር ውል ገብተዋል፡፡ በገቡት ውል መሰረትም ሌላ ሥራ ሳይሰሩ ደሞዝ እየተከፈላቸው ከሕዳር 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለሚቀጥሉት 6 ወራት 65 ሰዎች በቋሚነት ኢዜማን የሚያገልግሉ ይሆናል፡፡ የስልጠናው ተካፋዮች ዋነኛ የሥራ ድርሻቸው የሚሆነውም የሚያስተባብሯቸው የምርጫ ወረዳዎች የምርጫ ዘመቻን መሸከም የሚችሉበት ቁመና ላይ እንዲደርሱ ማድረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል